


# ልጆችን እና ቤተሰቦችን ለማገዝ የ DC የመጀመሪያ ትምህርት መለኪያዎች እና የርቀት ትምህርት መመሪያን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

በ ኮሮና ቫይረስ (COVID-19) የህዝብ ጤና ድንገተኛ ሁኔታ፣ ብዙ የቅድመ እንክብካቤ እና የትምህርት ፕሮግራሞች ለጊዜው ለመዝጋት ከባድ የሆነ ውሳኔ አደረጉ። ከውልደት እስከ 5 ዓመት ላሉት ልጆች  አቅራቢ፣ አስተማሪ ወይም ተንከባካቢ እንደመሆንዎ የርቀት ትምህርትን ሙሉ በሙሉ የተገበሩበት የመጀመሪያ ጊዜ ይህ ሊሆን ይችላል። ይህ እንዴት ማድረግ እንዳለብዎት የሚያሳይ መመሪያ የ**DC የመጀመሪያ ትምህርት መለኪያዎች (DC Early Learning Standards) (DC ELS) እና የርቀት ትምህርት መመሪያ ን ልጆችን እና ቤተሰቦችን ለመርዳት ይጠቅምዎታል።**

እነዚህ የDC ELS ማሻሻያዎች ልጆች ሊያውቋቸው እና ሊያደርጓቸው የሚችሉትን ነገሮች እና በተለያዩ እድሜዎች እና የእድገት ደረጃዎች ልጆች እንዴት እንደሚያድጉ ለወላጆች እና ለአስተማሪዎች ስለ ስለሚጠበቁ ነገሮች መረጃ  ይሰጣሉ። እነሱ በልጁ ላይ ሙሉ በሙሉ ያተኩራሉ እናም የህጻናትልጆች ትምህርት እና እድገት  እርስ በእርስ የተዛመዱ እና ሁሉንም የትምህርት ስፍራዎች ስለሚነኩ ሰፋ ያለ ማእቀፍ ያላቸውን ጎራዎችን ያካትታሉ። የDC ELS  መስፈርቶቹ ከ *Head Start Early Learning Outcomes Framework ጋር* የሚስተካከሉ ናቸው፣ *Ages Birth to Five* (2015)፣ the *Common Core State Standards for English Language Arts* እና*Mathematics* (2010) እንዲሁም the *Next Generation Science Standards* (2013)። አገልግሎት ሰጭዎች፣ አስተማሪዎች እና ተንከባካቢዎች ከመለኪያዎቹጋር የተዛመዱ ልምዶችን ተግባራዊ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በቤት ውስጥ ለመደገፍ መለኪያዎቹን በእንግሊዝኛ፣ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ፣ በፈረንሣይኛ፣ በኮሪያ፣ በ ቻይንኛ (ማንዳሪን) ወይም በ ቬትናምሚዝ እያጣቀሱ መጠቀም ይችላሉ። የሚከተለው አጭር እይታአንድ ምሳሌ ያሳያል፣

## *DC ELS አጭር እይታ*

ለደረጃ 6፣ እራስን ለመግለፅ ቋንቋን ይጠቀማል፣ አመላካቾችን፣ ምሳሌዎችን፣ ደጋፊ ልምዶችን እና *ከመደበኛ ቁልፍ የመንግስት መለኪያዎች ጋር* መጣጣምን ትኩረት ይሰጣል። የ DC ELS የትምህርት እቅድ እና መልመጃዎችን ለማዘጋጀት መነሻ የሚሆንዎትን በጥናት ላይ የተመሰረቱ ምሳሌዎችን እና አጋዥ ልምዶችን ይሰጣል።  በተጨማሪ እነዚህን ልምዶች ለርቀት ትምህርት  ቤተሰቦች እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ የእርሰን ድጋፍ እንደሚፈልጉ ማጤን ጠቃሚ ነው።




| ቅድም ትምህርት ቤት | ...ም መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | የታወቁ ዋና የመንግስት መለኪያዎች |
| 6a. የራሳቸውን ፍላጎቶች ለማሟላት እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማብራራት፣ ለመግለፅ እና ለማስተዳደር በዕለት ተዕለት ንግግር ውስጥ አዳዲስ ቃላቶችን ይጠቀማሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• "A caterpillar is in the cocoon." ["አባጨጓሬ በሸረሪት ድር ውስጥ ነው።"] ይበሉ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች ወደ ትምህርት ቤት መጓዝን ጨምሮ ስለእለትተለት መደበኛ ተግባሮቻቸው ታሪኮችን እንዲናገሩ ያበረታቱ። | **የእውቀት እና ሀሳቦች አቀራረብ**<br>6a. የሚታወቁ ሰዎችን፣ ቦታዎችን፣ ነገሮችን እና ክስተቶችን ይገልጻል እና በግፊት እና በድጋፍ፣ ተጨማሪ ዝርዝር ይሰጣሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ወደ ምግብ ሸቀጣሸቀጥ ያደረጋቹትን ጉዞ ተናገሩ፣ ሲጠየቁ የተወሰኑ እቃዎችን በመግለጽ፣ የመጡት ከፍሪጅ መሆኑን ይግለጹ።<br>6b. በግልጽ ለመረዳት በሚያስችል ሁኔታ፣ ሀሳቦችን እና ስሜቶችን በቃላት ይገልጻሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በአነስተኛ ቡድን ጊዜ፣ ለአንድ ተግባር የተሰጠውን መመሪያዎች በግልጽ ይድገሙ ምክንያቱም የክፍል ተማሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያልተረዱ መሆኑን ተናግረዋል።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች ጠዋት ሲመጡ፣ ወደ ትምህርት ቤት እንደመጡ እንዲናገሩ አድርጓቸው። ስለ ጉዞቸው ዝርዝር እንዲሰጡ ለማበረታታት ጥያቄዎችን ይጠይቁ (ለምሳሌ ፣ "Did you pass any stores? [" መደብሮችን አልፋችዋል?] Did you see any stop signs? [የማቆሚያ ምልክቶችን አይታችዋል?] Did you go when the light turned green?" [መብራቱ ወደ አረንጓዴ ሲለወጥ ሄዳቹ? "])።<br>• ልጆች የሚጠይቁትን ጥያቄዎች መረዳት ካልቻሉ ጥያቄያቸውን በሌላ መንገድ ለመጠየቅ እንዲያስቡ ያበረታቷቸው። | **የእውቀት እና ሀሳቦች አቀራረብ**<br>SL.K.4. የታወቁ ሰዎችን፣ ቦታዎችን፣ ነገሮችን እና ዝግጅቶችን መግለጽ እና በግፊት እና ድጋፍ፣ ተጨማሪ ዝርዝር ማቅረብ።<br>SL.K.5. እንደአስፈላጊነቱተጨማሪ ዝርዝሮችን ለመስጠት መግለጫዎች ላይ ስዕሎችን ወይም ሌሎች የእይታ ማሳያዎችን ይጨምሩ።<br>SL.K.6. በሚሰማ መልኩ መናገር እና እና ሀሳቦችን ፣ ስሜቶችን እና ሀሳቦችን በግልፅ ግለጽ።<br>**የቃላት እውቀት እና አጠቃቀም**<br>L.K.4. በመዋለ ሕጻናት ንባብ እና ይዘት ላይ በመመርኮዝ የማይታወቁ እና የባለብዙ-ትርጉም ቃላቶችን እና ሀረጎችን ትርጉም መወሰን ወይም ግልጽ ማድረግ።<br>• ለሚታወቁ ቃላት አዳዲስ ትርጉሞችን መለየት እና በትክክል መጠቀም (ለምሳሌ ፣ ዳክዬ ወፍ መሆንዋን ማወቅ እና "ዳክ" የሚለውን ግስ መማር) ። |

## የርቀት ትምህርት መመሪያ

የርቀት ትምህርት መመሪያው በቤት ውስጥ የሚማሩ ህጻናትን እና ቤተሰቦችን ለማገዝ የትምህርት እቅዶችን እና እንቅስቃሴዎችን እንዲያዘጋጁ ሊረዳዎ ይችላል። የተራዘመ የማያ ገጽ ጊዜ ለልጆች እድገት ተገቢ ባይሆንም፣ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በራሳቸው ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን እንቅስቃሴዎች እና ስልቶች ለማሳየት እንደ Microsoft Teams ወይም Google Meet ያሉ መድረኮችን



# ልጆችን እና ቤተሰቦችን ለማገዝ የ DC የመጀመሪያ ትምህርት መለኪያዎች እና የርቀት ትምህርት መመሪያን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

መጠቀም ይችላሉ። በ[የርቀት ትምህርት መመሪያ<} ገፅ ሁለት ላይ  ያለው፣የቤተሰብ ተሳትፎ  የሚለው የኦንላይን የትምህርትእቅድ ዝግጅት መሳሪያ የዚህን ስትራቴጂ አጠቃላይ እይታ የሚሰጥ እና በሚከተለው ገጽ ላይ ተጠቃሏል።]

- **ይወቁ፡** የDC ELS ን በመጠቀም ልጆችን እና ቤተሰቦችን በየትኛው መለኪያ ላይ ማገዝ እንደሚፈልጉ  ይለዩ። በርቀት ትምህርት ላይ በመመርኮዝ ድጋፍ ሰጭ ልምምዶች ላይ ምን አይነት ማስተካከያዎችን እንደሚያደርጉ ያስቡ። ከዚህ በፊት በክፍል ውስጥ የተገበሯቸውን ትምህርቶች እና እንቅስቃሴዎችን ያስቡ እና እነሱን ቤተሰቦች  በርቀት ትምህርት ግዜ ተግባር ላይ እንዲያውሉት እንዴት ሊያሻሽሉት እንደሚችሉ በሚገባ ያጢኑ።

- **ይመልከቱ፡** እንቅስቃሴውን ወይም ስትራቴጂውን ለማሳየት ከቤተሰብ ጋር በቡድን ወይም በተናጠል ጊዜ ያመቻቹ። መረጃውን ለማስተላለፍ የኦንላይንመድረኮችን፣ የስልክ ጥሪዎችን ወይም ሌሎች መንገዶችን ይጠቀሙ። በእንቅስቃሴው ወቅት ቤተሰቦች በቤት ውስጥ  ያሉ በብዛት ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን  ነገሮች በመለየት ያግዙአቸው።

- **ይሞክሩት**፣ ቤተሰቦች በቤት ውስጥ እንቅስቃሴዎችን እና ስልቶችን በየቀኑ እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው። ልጆቻቸው እንቅስቃሴዎቹ ላይ ያላቸው ምላሽ እና ተሳትፎን አስመልክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ቤተሰቦችን ይጠይቁ።

- **ይከልሱ**፣ በቤተሰቦች አስተያየት ላይ በመመርኮዝ፣ ድርጊቶቹ እና ስትራቴጂዎቹ ላይ ሊያደርጉት ስለሚችሉ ማሻሻያዎች፣ ወይም ማጋራት ለሚችሏቸው ማናቸውም ተጨማሪ ግብአቶችን ያሰላስሉ።

## *DISTANCE LEARNING RESOURCE GUIDE FOR LOCAL EDUCATION AGENCIES (ለአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች የርቀት ትምህርት ግብአት መመርያ) (LEAS)*

በተጨማሪ OSSE በግዛቱ ላሉ የህዝብ ትምህርት ቤቶች አስተዳዳሪዎችን እና አስተማሪዎችን ለመደገፍ፣ ለአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEAs) የርቀት ትምህርት ግብዓት መመሪያ አሳትሟል። ምንም እንኳን ለመጀመሪያ እንክብካቤ እና በትምህርት ኘሮግራሞች ላይ በተለየ መልኩ ታልመው የተዘጋጁ ባይሆኑም ፣ስልቶቹ በቤት ውስጥ ከልጆች እና ቤተሰቦች ጋር በተሳካ ሁኔታ እንዲሳተፉ ይረዱዎታል። የመረጃውን መመሪያ [በእንግሊዝኛ]፣ [በስፓኒሽኛ]፣ [በአማርኛ]፣ [በፈረንሣይኛ]፣ [በቪትናሜሴ]፣ [በኮሪያ] እና[በቻይንኛ] ማውረድ ይችላል።

## ከቤት በሚማሩበት ወቅት ቤተሰቦች ልጆችን እንዲደግፉ እንዴት መርዳት እችላለሁ?[i]

ቤተሰቦች ከልጆቻቸው ጋር አብረው የሚጠቀሙባቸውን የትምህርት እንቅስቃሴዎች እና ስልቶች ከማዘጋጀት እና ከማስማማት በተጨማሪ፣ ቤተሰቦች ጤናማ የሆኑ የተለመዱ አሰራሮችን እንዲመሰርቱ መርዳት ልጆችን ወደ የርቀት ትምህርት ለማሻገር በሚደረገው ለውጥ ላይ ሊረዳቸው ይችላል። ወላጆች ሊኖሩአቸው የሚችሉትን የሚከተሉትን የሚመሩ ጥያቄዎች እና እንዴት እነሱን መደገፍ እንደምትችሉ አስቡባቸው፣

| የመመርያ ጥያቄዎች | ተገቢ የሆኑ ግብአቶች | እነዚህን ግብአቶች መጠቀም የሚቻልባቸው መንገዶች |
|---|---|---|
| **ልጄን ለርቀት ትምህርት እንዴት ማዘጋጀት እችላለሁ?** | **የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጁ።** | አብዛኛው ልጆች በፕሮግራም ቀን የጊዜ ሰሌዳ ለምደዋል፣ ስለዚህ ተመሳሳይ አይነት ነገር በቤት ውስጥ መፍጠር ወደ ተለየ አይነት የትምህርት አካባቢ በቀላሉ እንዲሸጋገሩ ሊረዳ ይችላል። |
| | **የእረፍት ጊዜዎችን ያዘጋጁ እና የአካል እንቅስቃሴዎችን ያቅርቡ።** | ባህላዊ ት / ቤቶች እና የቅድመ-እንክብካቤ እና የትምህርት መርሃግብሮች የተወሰነ የዕረፍት ጊዜ ወይም ከቤት ውጭ ጊዜን ያካትታሉ፣  ስለዚህ የርቀት ትምህርት መርሐግብር የተለየ መሆን የለበትም። ከቤት ውጪ ጊዜ እና ንጹህ አየር ትልቅ የአካል እና የአእምሮ የጤና ጥቅሞች አሉት ። |



# ልጆችን እና ቤተሰቦችን ለማገዝ የ DC የመጀመሪያ ትምህርት መለኪያዎች እና የርቀት ትምህርት መመሪያን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

| | | |
|---|---|---|
| | **የእደጥበብ ይኑሮት።** | ሥነ-ጥበባት እና እንቅስቃሴን ማጎልመሻ እንቅስቃሴዎች የትምህርት አስፈላጊ አካል ናቸው። በቤት ውስጥ ከልጆች ጋር መሥራት ቤተሰቦችን እንዲፈጥሩ እና ኪነጥበብን እንዲጠቀሙ የማድረግ እድል ይሰጣቸዋል። |
| | **የእንቅልፍ ጊዜን ያክብሩ።** | ለልጆች አምሽተው መተኛት እና አርፍደው መነሳት ሊያጓጓቸው የሚችል ቢሆንም፣ ጤናማ የእንቅልፍ ጊዜን መቀየር ለአካል እና የአእምሮ ጤናቸው ጠቃሚ አይደለም። በቀን እንቅልፍ ጊዜን መጠበቅም እንዲሁ ለልጆች እድገት አስፈላጊ ነው። |
| | **መግባባት መቻል ቁልፍ ነው።** | ድጋፍ እንደተደረገላቸው እንደሆነ እንዲሰማቸው ከቤተሰቦች ጋር ግልጽ የሐሳብ ልውውጥ ያድርጉ። |

## ብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦች ልጆችን ቤት ውስጥ በሚማሩበት ጊዜ እንዲደግፉ እንዴት መርዳት እችላለሁ?[ii]

በመጀመሪያ እንክብካቤ እና በትምህርት መርሃ-ግብርዎ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው የመጀመሪያ ቋንቋ ቤተሰቦች በቤት ውስጥ ከሚጠቀሙባቸው የመጀመሪያ ቋንቋ (ዎች) የተለየ ሊሆን ይችላል -ከቤተሰቦች ጋር አጋርነት በመፍጠ የቋንቋ እና የባህል እሴቶች የልጆች የርቀት ትምህርትን እንዲደግፉ ይጠቀሙባቸው። ወላጆች ሊኖሩአቸው የሚችሉትን የሚከተሉትን የሚመሩ ጥያቄዎች እና እንዴት እነሱን መደገፍ እንደምትችሉ አስቡባቸው፣

| **የመመርያ ጥያቄዎች** | **ተገቢ የሆኑ ግብአቶች** | **እነዚህን ግብአቶች መጠቀም የሚቻልባቸው መንገዶች** |
|---|---|---|
| እኔ እንግሊዘኛ መናገር የማልችል ከሆነ፣ ልጄ ከቤት በሚማርበት ወቅት ምን እንደሚሰራ፣ እንደሚማር፣ እና እንደሚለማመድ እንዴት ላውቅ እችላለሁ? | ልጅዎ ቤት ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ ያለውን የመማሪያ እቅድ ለመረዳት እና ስለሚያስፈልገውን የቴክኖሎጂ ሁኔታ ለማወቅ፣ ከልጅዎ የመጀመሪያ እንክብካቤ እና የትምህርት ፕሮግራምጋር ግንኙነት ይኑሮት። | የኮንፈረንስ ስነስርአቶችን፣ ቀኖችን፣ እና ጊዜዎችን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የልጅዎን አስተማሪ ወይም ፕሮግራሙ ጋር ይደውሉ። የአስተማሪውን ኢሜይል ወይም ደግሞ ያለውን ሌላ የመገናኛ ቻነል (መንገድን) ማስቀመጥዎን እርግጠኛ ይሁኑ። |
| **ከልጆቼ ጋር በቤት ውስጥ በማሳልፍበት ጊዜ ልጆቼ ስሜታቸውን መግለጽ እንዲችሉ እንዴት ልረዳቸው እችላለሁ?** | ለልጅዎ ጆርናል ወይም ደግሞ ማስታወሻ ደብተር ይስጡ። በጆርናል ላይ መጻፍ፣ ስኬች ማድረግ፣ ወይም መሳል ወጣት ተማሪዎች በዚህ እርግጠኛ ባልሆነ ጊዜ ውስጥ ስሜቶቻቸውን እንዲያደምጡ ይረዳቸዋል። | ስለ ቫይረሱ እያንዳንዱ ሰው ምን እየተሰማው እና እንዴት እየተቋቋመው መሆኑን እንደቤተሰብ ለማውራት ጊዜ መመደብ ትችላላቹ። |
| **እኔ እንግሊዘኛ መናገር የማልችል ከሆነ የልጄን ስራዎች ለመከታተል ምን ማድረግ አለብኝ?** | የ DC ELS ቤተሰቦች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ የእድገት ምእራፎች አሉት። DC ELS በእንግሊዝኛ፣ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ፣ በኮሪያ፣ በቪትናሜሴ፣ በቻይንኛ (ማንዳሪን) እና ፈረንሳይኛ ታትሟል። ልጅዎ ከአስተማሪዎ ጋር በተመሳሳይ ክፍል ውስጥ አይደሉም። ለመርዳት እርስዎ ከልጅዎ ጋር በተመሳሳይ ክፍል ወይም እንግሊዘኛ መናገር እንዳለብዎ አያስቡ። | እርስዎ የታዘዘውን የትምህርት ይዘት እና/ወይም የትምህርት ስራዎች ላይ ለማውራት ጊዜ መመደብ ይችላሉ። ልጅዎ የወደዱትን የእሱን/የሷን ተግባር ምን እንደሆነ፣ የትኛውትኛው ተግባር ለማከናወን በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ፣ እና ምክንያቱን ይጠይቁ፣ |




# ልጆችን እና ቤተሰቦችን ለማገዝ የ DC የመጀመሪያ ትምህርት መለኪያዎች እና የርቀት ትምህርት መመሪያን

## ጁንዩ ሕ መጡቆመ ጁንዩመ ቿለ

| የመመርያ ጥያቄዎች | ተገቢ የሆኑ ግብአቶች | እነዚህን ግብአቶች መጠቀም የሚቻልባቸው መንገዶች |
|---|---|---|
| **እቤት ውስጥ እያለሁ ልጄን ለመርዳት፣ በልጄ የቅድመ እንክብካቤ እና የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ የሚጠቀመውን ቋንቋ መናገር አለብኝ?** | በልጅዎ የመጀመሪያእንክብካቤ እና የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ የሚጠቀሙበትን ቋንቋ መናገር አያስፈልግዎትም። እርስዎ ሀሳቦችዎን ለመግለጽ ወይም ደግሞ መመርያዎን ለመስጠት በጣም የሚመችዎትን ቋንቋ ሁሉጊዜ መጠቀም ይችላሉ። | እርስዎ ኤክስፐርት (ባለሞያ) መሆን አያስፈልግዎትም! ሊያደርጓቸው ከሚችሏቸው በጣም ደጋፊ ነገሮች ውስጥ አንዱ የልጅዎን ፍላጎቶች መደገፍነው። በሚያከናውኑበት ጊዜ የሚያስቡትን ነገር ጮክ ብለው ይናገሩ ወይም ይግለጹ፣ ማብሰል፣ አንድን ነገር መጠገን፣ የቤት ውስጥ እንስሳቶችን መንከባከብ፣ ወይም ሌላ የቤት ውስጥ ስራ መስራትን ሊሆን ይችላል። ጥያቄዎችን ይጠይቁ፣ መልሱን የማያውቁት ቢሆንም እንኳን! |

## ሙያዊ እድገት

ተጨማሪ ድጋፍ ይፈልጋሉ? የርቀት ትምህርት መመሪያው፣ በሞያዊ እድገት መረጃ ስርዓት (PDIS) ላይ የታተሙ የተሰራጩ ትምህርቶችን፣ በ Quorum እና Early Childhood Investigations ዌቢናሮች ላይ ያሉ ኦንላይን ኮርሶችን ጨምሮ ከሙያ የእድገት ግብአቶች ጋር ያገናኛዎታል። PDIS እና Quorum በግዛቱ የልጆች እድገት ማእከሎች እና ቤቶች ውስጥ ለሚሰሩ ለመጀመሪያልጅነት አስተማሪዎች እና ተንከባካቢዎች ነፃ ናቸው። ለ PDIS ወይም ለ Quorum ምዝገባ እርዳታ ከፈለጉ፣ የ Early Childhood Education (ECE) የድጋፍ ዴስክ በ ECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903 ያነጋግሩ።

---

ከDISTANCE LEARNING RESOURCE GUIDE FOR LOCAL EDUCATION AGENCIES (ለአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች የርቀት ትምህርት ግብአት መመርያ) ላይ የተወሰደ።

[ii] Ibid., ገፅ 2